# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ኤልሳዕ፣ የተዓምራት ሰው፡፡


ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ማረሻውን ለመሳብ በቂ የሆኑ በሬዎች አልነበሩም፡፡



አንድ ተጨማሪ ያስፈልግ ነበረ፡፡ ያ ግን ወጣቱን ገበሬ ኤልሳን አላገደውም ነበረ፡፡ እርሱ የቀረውን የአንዱን በሬ ቦታ በመተካት ከሌሎቹ በሬዎችጋ አንድ ላይ በቀላሉ ተቧድኖ ይሰራ ነበረ፡፡ እጅግ ጠንካራ ሰው መሆን አለበት ፤ ብልህና ጠንካራ ፣ ጎበዝ ሰራተኛም፡፡



ኤልሳዕ እያረሰ እያለ ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ኤልያስ መጣና ጠራው፡፡ ወጣቱ ሰው የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን ሲል እርሻውን ጥሎ ሄደ፡፡ አንድ ቀን ፣ እግዚአብሔር ኤልያስን በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወሰደው፡፡ ከዚያም ፣ ኤልሳዕ ለእስራኤል የእግዚአብሔር ነብይ ሆነ፡፡

3



ምንም እንኳን  ኤልያስ በመወሰዱ ኤልሳ ደስተኛ ባይሆንም፣ እግዚአብሔር እንደ ኤልያስ አይነት ኃይል እንዲሰጠው ብሎ ለመነ፡፡ ኤልሳም የኤልያስን መጎናጸፊያ ወሰደና ይፈስ የነበረውን ወንዝ እንደ ኤልያስ መታው፡፡

ውኃውም ተከፈለ ፤ ከዚያም ኤልሳ እግዚአብሔር ከእርሱጋ እንዳለ አወቀ፡፡

4



ኤልሳም ቤቴል ወደምትባል ከተማ ሲገባ ፣ “አንተ መላጣ ፣ ሂድ”  እያሉ ልጆች ይቀልዱበት ጀመረ ፡፡ ኤልሳ የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለመሆኑ ምንም ግድ አይሰጣቸውም ነበረ፡፡ እጅግ አስደንጋጭ ነገር በእነርሱ ላይ ተፈጠረ ፤ ሁለት ሴት ድቦች ከጫካ ውስጥ ወጥተው አርባ ሁለት የሚሆኑትን ልጆች ዋጡአቸው፡፡

5



አንድ ቀን ኤልሳ ዕዳ ያለባትንና መክፈል ያቃታትን ሴት አገኘ፡፡ ገንዘቡን ለማግኘት ሲል ፣ አበዳሪዋ የባልቴትዋን ሁለት ልጆች ባሪያ አድርጎ ሊወስዳቸው ተዘጋጅቷል፡፡ ኤልሳም እንዲህ አላት ፣ “ሂጂና ከጎረቤቶችሽ ባዶ ማድጋ ተዋሺ ፤..........”፡፡ እግዚአብሔር አንድ አስደናቂ የሆነ ነገር ለዚያች ሴት ማድረግ አስቦ ነበረ፡፡

6

ባልቴቷ በትንሽዬ እንስራ የተቀመጠ ዘይት ብቻ ነበራት፡፡ ነገር ግን ከዛች ትንሽ እንስራ ወደ እነዚያ ሁሉ ማድጋዎች ዘይት ሞላች፡፡ በነዚያ ዘመናት የመታጠቢያ ገንዳዎች ቢኖሩ ፣ እግዚአብሔር እነርሱን ሁሉ ሳይቀር ይሞላቸው እንደነበረ ታስባለህ ; ባልቴቷም ዘይቱን ሁሉ ሸጠችውና ልጆችዋን አዳነች፡፡



7

ሌላ አንዲት ሴትና ባሏ ፣ ኤልሳ በእነርሱ አከባቢ ሲያልፍ ሊያርፍባቸው የሚችል ልዩ ቤት አዘጋጁለት፡፡ በክፍሉም ውስጥ ፣ አልጋ ፣ ጠረጴዛ ፣ ወንበርና መቅረዝ አስቀመጡ፡፡ ያ ክፍል ሁልጊዜ ለኤልሳ የተጠበቀ ነበረ፡፡



8

ኤልሳም ይሄንን ውለታ እንዴት ሊከፍል እንደሚችል ሁልጊዜ ያስብ ነበር፡፡
ልጅ እንዳልነበራቸውም ሲያውቅ ፣ ሴቲቱ ማመን የማትችለውን አንድ ነገር
ነገራቸው፡፡ “በሚመጣው አመት በዚህን ሰዓት ልጅ ይኖራችኋል፡፡”
በእርግጥም ፣ ከአመት በኋላ ፣ ልጁ ተወለደ፡፡



9

ከጥቂት አመታት በኋላም ፣ ያው ልጅ ከአባቱጋ በሜዳ ነበረ፡፡ ልጁም
“ራሴን ፣ ራሴን” እያለ ይጮህ ጀመረ፡፡ ልጁንም ወደ እናቱ ይዘውት
ሲመጡ ፣ እስከ ከሰዓት ድረስ በእናቱ ጉልበት ላይ ነበረ ፤ ከዚያም ሞተ፡፡
እናቲቱም በኤልሳ ክፍል ውስጥ ባለ አልጋ ላይ አስቀመጠችው፡፡
ማን ይረዳታል ብለህ ታስባለህ?



10

ኤልሳ አልክ; ትክክል! በአህያ ላይ ተጭና እርሱን ፍለጋ ወጣች፡፡ ኤልሳም ወደ
ሴቲቱ ቤት መጣና ወደ ሰገነቱ ወጣ ፤ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ፡፡
እግዚአብሔርም ልጁን ዳግም ወደ ሕይወት መለሰው፡፡ ኤልሳም ሴቲቱን
ጠርቶ እንዲህ አላት ፣
“ልጅሽን ውሰጂ፡፡” እንዴት
ያለ ደስተኛ እንደምትሆን
አስብ!



11

በሶርያ አቅራቢያ ባለ ምድር የሚኖር
ንዕማን የሚባል የጦር አዛዥ ነበረ፡፡
እርሱም ጀግና እና ጠንካራ ሰው ነበረ ፤
ነገር ግን እጅግ አስጨናቂ የሆነ ለምጥ
የሚባል የቆዳ በሽታ ነበረበት፡፡



12

የንዕማንም ሚስት ከእስራኤል ምድር
የተማረከች ትንሽዬ ባሪያ ልጅ ነበረቻት፡፡
ይህች ትንሽ ሴት ፣ “ንዕማን በእስራኤል
ያለው ነብይጋ ቢሆን ፣ ይሄ ለምጥ
ይፈወስ ነበረ፡፡”



13

ንዕማን ነብዩን ለማየት ተነሳ፡፡ በፊቱም ለማቅረብ ፣
ብር ፣ ወርቅና እጅግ ያማረ ልብስ ያዘ፡፡



14



የኤልሳም አገልጋይ ወጣና
እንዲህ አለ ፤” ውጣና
በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ
ታጠብ ፤ ከዚያም ትነፃለህ፡፡”
ንዕማን እጅግ ተናድዶ ነበረ፡፡”
በምድሩ ባሉ ንጹህ ወንዞች
መታጠብ አይችልም ነበረ;
በብስጭት ወደ መጣበት ሃገር
ተመለሰ፡፡





እንደ ዕድል ሆኖ ለንዕማን ፣
ባሮቹ የኤላሳን ትዕዛዝ
እንዲሰማ ብለው ጠየቁት፡፡
በዚህም ምክንያት ፣ ንዕማን
ወረደና በዮርዳኖስ ወንዝ
ሰባት ጊዜ ታጠበ፡፡ ከዚያም
ለምጣሙ ንዕማን ነጻ!
ከዚያም ንዕማን
ለእውነተኛው አምላክ ፤
ለኤልሳ አምላክ ፤ ከለምጥ
ደዌ ላዳነው አምላክ ሰገደ፡፡





እግዚአብሔር አገልጋዩን ኤልሳን
ከሞተ በኋላ ፣ እንኳን
ተጠቅሞታል፡፡ አንድ ቀን ፣
ኤልሳ በተቀበረበት ዋሻ ውስጥ
አንድ ሰው ተቀብሮ ነበረ፡፡
የሞተው ሰው አካል የኤልሳን
አስከሬን አጥንቶች ሲነካ፣
ሰውየው ተነቃቃና በእግሮቹ
ቆመ፡፡ በእርግጥም ፣
እግዚአብሔር የኃይሉን ታላቅነት
ታማኝ በሆነው በአገልጋዩ
በኤልሳ በኩል ገለጠ፡፡



ኤልሳዕ፣ የተዓምራት ሰው፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል**
**በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

2ኛ ነገስት 2 -13

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
***መዝሙረ ዳዊት* 119:130**






25

60



**ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው፡፡**

**እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል፡፡ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል፡፡ ደግሞም ያደርገዋል፡፡ እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን፡፡**

**ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ሰትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ፡፡ እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ፡፡ ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ፡፡ አሜን፡፡**

**በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር!** የሐ. 3.16